በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*ነሐሴ 22, 2007ዓ.ም*

# ***<u>የወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ውጤትና አንደምታው።</u>***

*በሀገራችን በኢትዮጵያ ለአምስተኛ ጊዜ የተካሄደው የይስሙላ አገርአቀፍ የሕዝብ ተወካዮችና የክልል ም/ቤቶች ምርጫ ካለፉት ምርጫዎች ጋር ሲነፃፀር የምርጫ ምህዳሩ ዝግ የሆነበት ፣ ግድያ፣እስራት ፣ አፈና፣ ወከባና ድብደባ የተፈጸሙበት አስፈሪና አሰቃቂ የሆነ ሕገወጥ የምርጫ ሂደት ነው።ለዴሞክራሲ ለሰብአዊ መብት መከበር ለመልካም አስተዳደርም ሆነ ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት ደንታቢስ የሆነው አምባገነን የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ነፃ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በማካሄድ ስልጣኑን በሰላማዊ መንገድ ያስረክባል ብሎ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ ይፈለፈላል ብሎ የማመን ያህል ነው።*

*ቀድሞውኑ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሃሰብን በጽሑፍም ሆነ በመናገር የመግለጽ መብት በተጨፈለቀበት ፣ የመገናኛ ዘዴው ( ሚዲያው)በአፋኙና በጨቋኙ ገዥ መደብ ቁጥጥር ስር በሚኙበት ፣የምርጫ ቦርድ፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች ሙሉ በሙሉ የኢህአዴግ ካድሬዎችና ደጋፊዎች በሆኑበት ሕዝቡ አማራጭ ሃሳቦችን ሰምቶ የራሱን ነፃ ውሳኔ ለመስጠት አልታደለም። ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮችና ሃገር በቀል የሲቪክ ማህበራት አልተሳታፉበትም። ገለልተኛ የሆነ ፍ/ቤት የለም።አምባገነኑ ሥርዓት የምርጫ ኮማንድ ፖስት አቋቋሞ የምርጫ ሂደቱን ለማፈንና ለመቆጣጠር ተንቀሳቅሷል።ያገዛዙ የአፈና መዋቅሮች ማለትም የጸጥታና የደህንነት ሀይሉ በአጠቃላይ መንግሥታዊ መዋቅሩ ፣ ሀብትና ንብረቱ ለወያኔ/ኢህአዴግ ምርጫ ቅስቀሳ አካልና ኢጋዥ ሆነዋል።ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጽህፈት ቤት ከፍተው በህዝብ ውስጥ ያለ ስጋት ተንቀሳቅሰው አላማና ፕሮግራማቸውን እንዳያስተዋውቁ ገደብ ተጥሎባቸው ከዚያም ላይ ዜጎች የተቃውሞ ሃሳብ ከሚያራምዱ ግለሰቦች ጋር የተጨባበጡ፣አብረው የተቀመጡ፣ የተነጋገሩ፣ቤታቸውን ያከራዩ ሁሉ ዛቻ፣ ማስፈራሪያ፣ ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው በዚህም ሳቢያ ሕዝቡ በፍርሃት አለም እንዲኖር እየተደረገ ባለባት ሃገር እንዴት ብሎ ነው ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማሰብ የሚቻለው?!*

*የሰላማዊ ትግሉ ዝግ በሆነባት ኢትዮጵያ ወያኔ/ኢህአዴግ የግንቦት 16 ቀን 2007 ዓ.ም ሃገር አቀፍ ምርጫ ተብዬን ያሸነፈው በቅድመ ምርጫ ወቅት ነው። ለአሸናፊነቱም ማሳያ ( ማረጋገጫ) ሊሆን የሚችለው የስርዓቱ አካልና ጉዳይ አስፈጻሚ የሆነው የምርጫ ቦርድ በአንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ( (አንድነት) እና በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መ.ኢ.አ.ድ) የቀረበለትን የውህደት ጥያቄ በኢ-ምክንያታዊ መንገድ አልቀበልም ከማለት አልፎ ሁለቱን ፓርቲዎች ያፈረሰበት ድርጊት፣ ለዩኒቨርስቲና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ፣ ለመንግሥት ሰራተኞች ጭምር ከፍተኛ የሃገር ሀብትና ንብረት በማፍሰስ ስለልማታዊ መንግሥትነቱ የሰበከበት በስልጠና ተብዬ የውሸት ፕሮፖጋንዳው የምረጡኝ ዘመቻ ያካሄደበት በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከምርጫው በፊት በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ እንዳያካሄዱ መደብደብ፣ ማሰር፣ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ማሳደድና ማፈናቀል ፣ ንብረታቸውን መውረስ፣ የምርጫ ምልክታቸውን (ፖስተር) ገንዘብ ከፍሎ ባሰማራቸው ቅጥረኞች ደጋፊዎቹ ማስቀደድ ፣ ዛቻና ማስፈራረት ማድረስ ሕዝቡ ነፃ አስተሳሰቡንና በነፃነት የመምረጥ መብቱን እንዳይጠቀም አንድ ለአምስት በሚባል ኮሚኒስታዊ አደረጃጀት አስሮና ጠርንፎ በመያዝ በቡና ጠጡ ፕሮግራም በየሰፈሩ ንብን ብቻ እንዲመርጡ በማስገደድና ቤት ለቤት እየዞሩ በማስፈረም በሕዝብ ላይ የፈጠሩት የፍርሃት ድባብ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም በመስጠትና በገንዘብ በመደለል የፈጸሙት አሳፋሪና አይን ያወጣ ተግባር ሃይሉን ( ጉልበቱን) ተጠቅሞ አሸናፊነቱን ለማወጅ መቁረጡን ጠቋሚ እንደነበር መገንዘብ ተችሏል።*

*ወያኔ/ኢህአዴግ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተለይም ሰማያዊ ፓርቲ (አይ ኤስ አይ ኤስ) ISIS ነው እርሱ ከተመረጠ ይጨፈጭፈችኋል ፣ ይጨርሳችኋል፣ ያርዳችኋል፣ እያለ የስም ማጥፋት የውሸት ፕሮፖጋንዳ ነዝተዋል።ክርስትናን አጥፍቶ የእስላም መንግሥት ሊያቋቁም ነው በማለት የክርስትና ዕምነት ተከታዮችን ቀስቅሷል፤ ለሙስሊሙ ሀብረተሰብ ደግሞ የእስልምና እምነትን አጥፍቶ የክርስትና እምነት ሊጭንባችሁ ነው በማለት በሁለቱም እምነት ተከታዮች መካከል መተማመን እንዳይኖር ያደረገው ጥረት የ1997ዓ.ም ኢንተርህሞዊይ ተብሎ የተነገረውን*

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*ያስታውሰናል። ገዢው ፓርቲ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በጠላትነት ፈርጆ ጥላሸት መቀባቱና ሕዝቡ ተቃዋሚዎችን እንዲፈራቸው ለማድረግ ሌት ተቀን መስራቱ የጸጥታና የደህንነት ሃይሉ ፀረ-ሰላም የሚላቸው ተቃዋሚ ሃይሎች ምርጫው በሰላም እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉትን አፍራሽ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና ምርጫው በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ተገቢውን ስልጠና ለመከላከያው፣ ለፖሊሱ፣ለደህንነቱ ፣ ለልዩ ሀይሉና ለሚሊሻው ሰጥተናል በቂም ዝግጅት አድርገናል እያሉ የገዥው ፓርቲ የጦር አበጋዞች በፕሮፖጋንዳ ማሽናቸው ሕዝብን ሲያስፈራሩና ሲያሸብሩ መክረማቸው ያለምንም ጥርጥር የኢህአዴግን በጉልበትና በአፈና የሕዝብን ድምፅ ቀምቶ የስልጣን እድሜውን በይስሙላ ምርጫ ለማራጋገጥ የቆረጠ መሆኑን አመላካች ነበር።*

***<u>በምርጫው እለት</u>*** *ከታዩና የምርጫውን ሕገወጥነት አመላካች ከሆኑ አሳፋሪ ድርጊቶች መካከል ለመጥቀስ ያህል በሁሉም የሃገሪቱ የምርጫ ክልሎች የተቃዋሚ ፓርቲ የምርጫ ታዛቢ ወኪሎች ምርጫውን እንዳይታዘቡ የተባረሩ፣ የታሰሩ፣ ምርጫው እስኪያበቃ ድረስ ታስረው የተፈቱ፣የተደበደቡ፣ በድብደባ በደረሰባቸው ጉዳት ሆስፒታል የገቡ፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች ዕጩ ተወዳዳሪዎች* ***<u>"ማንኛዉም ዕጩ ተወዳዳሪ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር አይያዝም ፣ አይታሰርም"</u>*** *የሚለው_የዕጩ ተወዳዳሪ የሕግ ከለላ ወይም ያለመከሰስ መብት ተጥሶ የታሰሩ፣ የታፈኑ፣ የተሰደዱ የተደበደቡ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፣ የት እንደደረሱ አድራሻቸዉ የማይታወቅ፣ ንብረት የተወረሰባቸውን ቤት ይቁጠረው።*

*በምርጫው እለት የድምፅ መስጫ ኮረጆ ተፈትሾ ባዶ መሆኑ ሳይረጋገጥ ድምፅ የተሰጠበት፣ ከድምፅ መስጠት በፊት በግማሽ በድምፅ መስጫ ወረቀት ኮረጆዎች የተሞሉበት፣ የተፎካካሪ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ምልክት ለመራጩ ሕዝብ ገለፃ ያልተደረገበት፣ንብ ላይ ብቻ ምልክት አድርጉ በማለት ምርጫ አስፈጻሚ ተብዬዎች መራጩን ሕዝብ ያስገደዱበት፣ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ካድሬዎች በምስጥር ድምፅ የሚሰጥበት ክፍል ተቀምጠው ከመራጩ ሕዝብ የድምፅ መስጫ ወረቀት እየተቀበሉ የኢህአዴግ  የምርጫ ምልክት በሆነው ንብ ላይ ምልክት እያደረጉ ኮረጆ እንዲያስገባ ያደረጉበት፣ ለታማኝ ካድሬዎቻቸው ካንድ የድምፅ መስጫ ወረቀት በላይ በመስጠት ደጋግመዉ እንዲመርጡ የተደረገበት፣ በዚህም ለመምረጥ ከተመዘገበው ቁጥር በላይ ውጤት የተገለፀበት ፣ የምረጡኝ ቅስቅሳ በተከለከለበት የምርጫ እለት የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች በየቤቱ እየዞሩና በምርጫ ጣቢያው በቅርብ ርቀት በመንገድ ዳር ሆነው የምርጫ ቅስቀሳ ያካሄዱበት፣ ከባድ መሳሪያ በተጠመደበት መኪና ላይ የተጫኑ ወታደሮች በድምፅ መስጫ ጣቢያ ፊትና ኋላ በመሆን መራጩን ሕዝብ በማስፈራራት በነፃነት እንዳይመርጥ ተጽእኖ ያሳደሩበት፣አዲስ የምርጫ ካርድ ለታማኝ ካድሬዎቻቸው በምርጫው እለት በመስጠት ድምፅ እንዲሰጡ የተደረገበት፣ ጸያፉና አሳፋሪ የምርጫ ደንብ ጥሰትና ግድፋት የተፈጸመበት ህገ ወጥ የሆነ የይስሙላ ምርጫ  ተካሄዷል።*

*የ2007 ዓ.ም የግንቦት ወር የወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ድራማ ወደኋላ መለስ ብለን በአገሪቱ የተተከለዉ የጎሳ ፖለቲካ ጅማሮና ቅንቀናው ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲው በአንድ ፓርቲ የንግድ ተቋማት መማከሉ ፣ የሲቪል ማህበራት በፓርቲው እዝ ስር እንዲወድቁ መደረጉ፣ የትምህርት ፖሊሲው አንድ ትውልድ አምክኖ ለሰደትና ለስራ አጥነት መዳረጉ፣ የአገር ሉዓላዊነት መገሰሱ፣ የሕዝብ አንድነት መላለቱ፣ የፍትህ ሥርዓቱ በሚያሳፍርና በሚያሳዝን ሁኔታ በሹመኞች ተረግጦ የማይሰራ ኩልሽ መሆኑ--------ያጋጠመንን የጨለማ ጉዞ ጠቋሚ ነበር። ይህ አደጋ የታያቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ብሔራዊ እርቅ ይፈጠር ፣ የሽግግር (የባለአደራ) መንግሥት ይቋቋም ፣ የአገር ሽማግሌዎች ተሳትፎ ለችግሮች የመፍትሔ አካል ይሁን ---እያሉ  ቢወተውቱ ባለጊዜዎች እነማን ተጣሉና የሚል ፌዝና ሌላ ሌላ ሰንካላ ምክንያት እየፈጠሩ በማጣጠላቸው ነገሮች ከድጡ ወደ ማጡ እንዲጓዙ ሆኗል።*

*የ2007ዓ.ም የምርጫ ድራማ አንደምታው ላለፉት ሰንከሳር የሕዝብ ሰቆቃ ፣ የአገር መቆረስና ዳር ድንባር መደፈር፣ የመሬት ቅርምት ፣ ኢትዮጵያን የመበታተን ተልዕኮውና ሌላው ሌላው ሁሉ አበሳ እንደሚቀጥል ነው የሚያሳያው። ወያኔ ከተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በነፃ ተወዳድሮ ቢሸነፍ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ ያስረክባል ተብሎ ማሰብም፣መመኘትም፣እንደማይቻል ከ1997ዓ.ም ጀምሮ በተካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ ታይቷል። የ2007ቱ የምርጫ ድራማ የወያኔ የሕዝብ ንቀቱ ፣ የፋሺስትነቱ ፣ የአገር አጥፊነቱ ምናልበትም የውድቀቱ የመጨረሻ ምዕራፍ ይሆናል።*

*ከዚህ የይስሙላ ምርጫ ጋር በተያያዘ በድህረ ምርጫ ዋናዋና የሚባሉ የተቀዋሚ  ፓርቲዎች የምርጫውን ውጤት እንደማይቀበሉት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ህብረተሰብ አሳውቀዋል።የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህን የአፈናና በኃይል እርምጃ የተጠናቀቀ ምርጫ ውጤት በዝምታ መመልከቱ የተዳፈነ እሳት እንዳለ ያሳያል። ሌላው ሊሳምርበት የሚገባ ጉዳይ ተቀዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አገርን ከውድቀት ለማዳን በሚደረገው ግብግብ መለስተኛ የሆኑ ቅራኔዎቻቸውን አቻችለው መዋሃድና አንድ ኃይል ሆነው አለመውጣታቸው ፣በአደረጃጀትም ከላይ እስከ ታች ወደ ሕዝብ ዘልቀው ኃይላቸውን በማጎልበት ገዢውን ፓርቲ ለድርድር ለማምጣት*

*ብሎም ለማንበርከክ የሚያስችላቸውን ሁኔታና አቅም መፍጠር ያለመቻላቸው የከፈሉትንና እየከፈሉ ያሉትን መስዋዕትነት ጎድቷል።*

*የግንቦት ወር የ2007ዓ.ም የይስሙላ ምርጫ ሌላ አንድምታ የሰላማዊ ትግሉ ማክተሙንና ሕዝባዊ አመጽ አይቀሬነቱን ማመላከቱ ነው።የሕዝብ እምቢተኝነትና አመጽ መካሄድ ያለበትም በተወሰኑ አካባቢዎች በሚፈጠሩ ክስተቶች ቀስቃሽነት ተጀምረው ቦግ እልም የሚሉ ሳይሆኑ መላ የአገሪቱን ሕዝቦች ከዳር እስከዳር ሊያነሳሱና ሕዝባዊ ማዕበል ሊፈጥሩ በሚችሉ ብሔራዊ የትግል ጥሪ መሆን አለበት።ይህ ካልሆነ በየቦታው በተነጠል የሚደረጉትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ወያኔ በግል እንዲያጠቃ አመቺ ይሆናል።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን የእምቢተኝነት አመጽ ለማካሄድ አስገዳጅ ሁኔታዎች ከበቂ በላይ ናቸው።ከዚህ ወዲያ ራሱን ለባርነት የሚያዘጋጅ ዜጋ መኖር የለበትም። መምህራን ይህን ወቅት አገርና ሕዝብ በማዳን መርህ ተንቀሳቅሰው እንዲሰሩ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ እያሳሰበ ባጠቃላይ ሕዝቡ የአገሩን ሉዓላዊነት ለማስከበር ፣ አንድነቱን ለማጥበቅ፣ ሰላምና ነፃነቱን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እንዲነሳ ጥሪ ያቀርባል።*

*ምርጫ ብሎ ነገር ቀልድ ነው፤ወያኔ የአገርና የሕዝብ ጠላት ነው!!*
*ለሕዝባዊ አመጽ በአንድነት እንነሳ!!*